# በአገራችን የተጀመረዉ የልማትና የማህበራዊ ግንባታ በሽብርተኞች ሴራ አይገታም::

የአገራችን ህዝብና መንግስት የችግሮቻችን መንስኤ በሆነዉ ድህነትንና ሓላቀርነትን ለማስወገድ በመካሄድ ላይ ያለዉ ባለ ብዙ ዘርፍ ትግል በተከታታይ ያስመዝገበዉ ከፍተኛ ዉጤት የሚያበረታታ ነዉ።

ይህ መልካም ጅማሮ የሚያመጣዉን ዘለቄታዊ ጠቀሜታ የተረዱ ኢትዮጵያዉያን በአንድነት እጅ ለእጅ ተያይዘዉ ወደፊት ባሉበት በአሁኑ ወቅት የአገራችን ለዉጥና ግስጋሴ ያሰጋቸዉ ወገኖች የተጀመሩትን የልማት ዉጥኖችና ዉጤቶች ቢቻል ለመደምሰስ ካልተቻለም ወደፊት እንዳይራመድ ለማስቆም ባለ በሌለ ሓይላቸዉ በመወረጨት ላይ ይገኛሉ።

የፀረ-ሰላምና የፀረ-ዕድገት ሐይሎች በሻብያ አስተባባሪነት የአገራችን ህዝብና መንግስት የጀመረዉን በጎ የልማትና የዲሞክራሲ ተግባራት አጠናክረዉ በመቀጠል ድህነትን ታሪክ እንዳያደርጉ የልጠነሰሱት ሴራ ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም።

አገራችን በማያባራ ጦርነት ዉስጥ እንድትዘፈቅ አንዴ በሰሜን በቅርቡ ደግሞ በምስራቅ የሀገራችን ክልል ተሞክሮ የነበረዉን የአክራሪ እስልምና አመራር የወረራ ተግባር በጀግናዉ የኢትዮጵያ ህዝብ የመከላከያ ሰራዊታችንና፣ በፀጥታ ሓይሎች እንዲመክን መደረጉ በእጅጉ የምያኮራ ተግባር ነዉ።

በቅርቡ በሻብያ አስተባባሪነት በኣፋር ክልል የታገቱ የዉጭ ዜጎችና ኢትዮጵያዉያን ላይ የተፈፀመ የሽብር ተግባር ሰላማችንና እድገታችን ለማደፍረስ ፀረ-ሰላምና፣ ፀረ-ዕድገት ሓይሎች፣ ምንኛ ቆርጠዉ እንደተነሱ የምያመላክት ሲሆን፣ ይህንን ተግባር በማክሸፉ ረገድ በመንግስታችን በኩል የተወሰደዉ ጥበብና ትዕግስት የተሞላዉ ቁርጠኛ አቋም፣ ታጋቶችን በማስለቀቅ ድርጊታቸዉን ማክሸፍ ተችለዋል።

ሚያዝያ 23/2007(እኤአ) በአገራችን የሱማሌ ክልል በደጋሀቡር ዞን አቡሌ በተባለ ቦታ በሽቢያ ግንባር ቀደም አጋፋሪነትና፣ ኤኤፍዲ በተባለ በሚጠራዉ የጀሌዎች ስብሰብ አባል በሆነዉ የኦጋዴን ነፃ አዉጭ ነኝ ባዩ ድርጅት፣ ተላላኪነት ሰላማዊ በሆኑ የልማት ሰራተኞች ላይ የተካሄደዉ እጅግ ኣሳዛኝና ዘግናኝ ጭፍጨፋ የ65 ኢትዮጵያዉያንና የ9 የቻይና ዜጎች ሕይወት በመቅጠፍና ለብዙ ንብረት መዉደም ምክንያት ሆነዋል።

በመሆኑም እኛ  የኢትዮጵያ ፍረም ፎር ፖለቲካል ስቢሊቲ (EFFPC)የዉይይት መድረክ እድምተኞች በሻብያ አጋፋሪነትና በጀሌዎች ፈፃሚነት፣ በወገኖቻችን ላይና በልማት አጋሮቻችን በሆኑት የቻይና ንፁሀን ዜጎች ላይ የተፈፀመዉን አረመናዊ ተግባር በመቃወም፣ ለሁለት ተከታታይ ቀናት ሚያዝያ 18 ና 19/1999 ዓ.ም ተገናኝተን በስፋትና በጥልቀት ዉይይት አድርገናል።

ስለ ሁናቴዉ ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት ባደረግነዉ ጥረት፣ የክልሉን ፕሬዚደንት የተከበሩ አቶ አብዱላሂ ሀሰን በቀጥታ ወደ መድረኩ ቀርበዉ በሰጡን ሰፋ የለ መግለጫ ሰፊ ግንዛቤ እንድንጨብጥ ረድቶናል።

በመጨረሻም የዉይይት መድረኩ አባላት በተስማሙበት መሠረት በወገኖቻችን ላይ ጭፍጨፋ ባካሄዱት ሽብርተኞችና ጀሌዎቻቸዉ ላይ የጋራ አቋም መግለጫ እንዲወጣ በተስማማነዉ መሠረት ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘረዉን የአቋም መግለጫ አዉጥተናል።

1ኛ በሱማሌ ክልል በደጋሀቡር ዞን ልዩ ስሙ አቦሌ በተባለ ስፍራ ተሰማርተዉ ለአገራችን ልማት ዋነኛ በሆነዉ ነዳጅ ፍለጋና ማዉጣት ተግባር ላይ የተሰማሩ ወገኖቻችን ላይ የተፈፀመዉን ኢሰብአዊ ጭካኔ የተሞላዉን ጭፍጨፋ በሙሉ ድምፅ እናወግዛለን።

2ኛ ከሱማሌ ክልል ፕሬዚደንት ከተከበሩ አቶ አብዱላሂ ሀሰን በተደረገልን ገለፃ መሠረት እነኚህ የልማት ሠራተኞች በተኙበት ፍፁም ሰብአዊነት በጎደለዉ መልኩ የተከናወነዉን ጭፍጨፋ በእጅጉ ያሳዘነን ብቻ ሳይሆን የስቀጣን ስለሆነ መንግስት እነኚህን ሽብርተኞችና ጀሌዎቻቸዉን ተከታትሎ በማደን ለፍርድ እንያደቀርብ እንጠይቃለን።

3ኛ የኢትዮጵያ የልማትና የዲሞክራሲ እድገት በፍፁም ላለማየት የወሰነዉ ሽብርተኛዉ የሻቢያ አጉራ ጠን አሸባሪ ቡድን በተለያዩ ጊዚያት በፈፀመዉ የሽብር ተግባርና ጠለፋዎች የእንግሊዝ፣ የፈረንሳይ፣ አሁን ደግሞ የቻይና፣ ዜጎች ጉዳት ደረሶባቸዋል፣ በመሆኑም ሻቢያ ከዚህ ዓይነቱ የጥፋት ተልዕኮ እንዲገታ ለማድረግ በመንግስታችን በኩል በሚገባዉ ቋንቋ እንዲነገረዉ አበክረን እናሳስባለን!

4ኛ በዚህ የሽብር ሰለባ ለሆኑት ኢትዮጵያዉያን ወነኖቻችን በተለይም ቤተሰቦቻቸዉ ላይ የደረሰዉ አስደንጋጭ ጉዳት የሳዘነን መሆኑን እየገለፅን እነኚህን ቤተሰቦች ለማበረታታት በኢትዮጵያ መንግስትም ሆነ በኢትዮጵያ ህዝብ የተዘጋጀ ሁኔታ ካለ አስፈላጊዉን ሁሉ ለማድረግ ቃል ገብተናል።

5ኛ ለምናከናዉነዉ የልማት ተግባር ከጎናችን ቆመዉ ያሉትን የቻይና ዜጎች ላይ የደረሰዉን ጉዳት በእጅጉ የሳዘነን ስለሆነ፣ በመንግስታችን በኩል ይህ ሀዘናችን ለመላዉ ቤተሰቦቻቸዉና ለቻይና መንግሰትና ህዝብ እንዲተላለፍ ተስማምተናል።

6ኛ የዚህ ሽብር ሰለባ ለሆነዉ የሱማሌ ክልል ህዝብ ከልማት ተግባሩ ለማስተጓገል የተፈፀመ ሴራ መሆኑን ተገንዝቦ ሽብርንና ሽብርተኝነት በመዋጋት ቀጣይ ወደሆነዉ የልማት ተግባር ትኩረቱን ሁሉ እንድያስተባብር እየጠየቅን ለክልሉ ነዋሪዎች ያለንን የትግል አጋርነት እናረጋግጣለን።

7ኛ ከአስመራ እስከ ፓርላማ ወይንም ደግሞ ከሞቋድሾ እስከ ፓርላማ ያለዉን ፀረ-ሰላምና፣ የፀረ-እድገትን ሴራ ለመባጣጠስ የተወካዮች ምክርቤት የስተላለፈዉን ወሳኔ አንቀፅ "ሐ" በተገቢዉ መንገድ ተግባራዊ እንዲሆን እየጠየቅን እኛም በቡኩላችን ለማድረግ የምንችለዉን ሁሉ ለመፈፀም በሙሉ ድምፅ ተስማምተናል።

8ኛ የዓለም አቀፍ ህበረተሰብ በሻቢያ አስተባባሪነት በተደጋጋሚ በአገራችን ላይ እየተፈፀመ ያለዉን የሽብርተኝነት እንቅስቃሴ በመረዳት በዚህ ተስፋ የቆረጠ መንግስት ላይ የተባበሩት መንግሰታት፣ የአዉሮፓ ፓርላማ፣ የአሜሪካን መንግስት፣የአፍሪካ ህብረት አስፈላጊዉን ጫና እንዲያደርጉ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

9ኛ በሻቢያ አሸባሪ መረብ ሰር የተሰባሰቡ እራሳቸዉን ኤኤፍዲ ብለዉ የሚጠሩ ብዱኖች፣ በወገኖቻችን ላይ የደረሰዉን ኢሰብአዊ ጭፍጨፋ ላይ ያላቸዉን ግልፅ አቋም እስካሁን የለማሳወቃቸዉ እኛን የሳዘነን ሲሆን፣ በአገር ቤትም ሆነ በዉጭ ያሉ የተቃዋሚ ቡዱን

አባላት ነን የሚሉ ሐይሎች በወገኖቻችን ላይ በደረሰዉ አሳዛኝ ድርጊት ላይ የላቸዉን ግልፅ አቋም እንዲያሳዉቁ እንጠይቃለን።

10ኛ የአሜሪካ መንግስት በዓለም-ዓቀፍ የፀረ-ሽብር ትግል ዉስጥ የምጫወተዉን ሚና እያደነቅን ነገር ግን በቅርቡ ባንዳንድ ሓላፊነት በጎደላቸዉ የኮንግረስ አባላት እየተገፋ ያለዉ፣ ኮኦልሽን ፎር (HR) 2003 የሚባለዉ፣ የኦጋዴን ነፃ አዉጭ ድርጅትን እንደ ዲሞክራሲያዊ ሓይል የሚቀበል መግለጫ፣ በእጅጉ የሳዘነን ብቻ ሳይሆን የስቆጣን ሙከራ ስለሆነ፣ ይህንን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ የሚራራጡ ወገኖች ከዚህ ተግባራቸዉ እንዲቆጠቡ እየጠየቅን፣ (HR)2003 እንዳያልፍ በምደረገዉ ሁሉ ዓቀፍ እንቅስቃሴ የበኩላቸንን አስተዋፅኦ ለማድረግ መንቀሳቀስ ያለብን መሆኑን ተስማምተናል።

11ኛ የተቛዋሚ ድርጅቶች የዜና ማግለጫ ተቛሞች በወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ያለዉን ጭፍጨፋ በመደገፍ በማጋነን የሚያስተላልፉት ፀረ-ህዝብ፣ ፀረ-ኢትዮጵያ ተግባር፣ በእጅጉ የሳዛነን ስለሆነ እነኚህ ሬዲዮ ጣቢያዎች ድህረ ገፆች የወይይት መድረኮች ከዚህ እኩይ ተግባራቸዉ እንዲታቀቡ እየጠየቅን፣ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ እንዲያወግዛቸዉ የትግል ጥሪ እናደርጋለን።

12ኛ ከኢትዮጵያ ወደ ዉጭ አገር እየተላለፈ ያለዉ የቴሌቢዠን ፕሮግራም ሆነ ልሎች የዜና ማሰራጫ መሣሪያዎች፣ የሻቢያ መንግሰትና ጀሌዎች ለ 24 ሰዓት/ 7ቀናት፣ እያከናወኑት ያሉትን የማያባራ የፀረ-ኢትዮጵያ ፕሮፖጋንዳ ለመምታት በሚየስችል ሁኔታ እንዲጠናከር እየጠየቅን፣ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት የበኩላችን አስተዋፅኦ ለማበርከት ቃል እንገባለን።

የሽብርተኞችና የጀሌዎቻቸዉ ሴራ ይክሽፋል
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!
ሚያዚያ 19/1999

የኢትዮጵያ ፎረም የፖለቲካ ሲቢሊቲ የዉይይት መድረክ ዕድምተኞች